# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
# ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:-aeup@ethionet.et


ቁጥር
Ref. No. መኢአድ/3/784/2
ቀን
Date 15/10/2002

**<u>እልህ አስጨራሽ ትግል የተካሄደበት እና አያሌ መስዋዕትነት የተከፈለበት ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ትግል በጉልበተኞች እና እውነትን ለመመስከር ባልፈለጉ ኃይሎች አይቀለበስም!!</u>**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባሳለፍነው ረዥም የመንግሥት ሥርዓት ሲታገልለት የኖረው የሕዝብ ስልጣን አመንጭነት፣ ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነትን መብት ለማረጋገጥ በሀገራችን ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ግንቦት 15/2002 ዓ.ም መካሄዱ ይታወቃል።

በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫው ግልጽ፣ ነጻ፣ ፍትሐዊ፣ ሰላማዊ፣ ሕጋዊና ዲሞክራሲያዊ እንዲሁም በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እንደሚሆን የነበረው ጥርጣሬ እንደተጠበቀ ሆኖ ሙሉ እምነት ነበረው።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ" የምርጫውን ሂደትና ውጤት የሚያሰናክሉና የሚያበላሹ የተለያዩ ድርጊቶች በመከሰታቸው ችግሮቹ በአስቸኳይ ተወግደው ምርጫው ያለምንም ተጽዕኖ እንዲከናወን ለኢትዮጵያ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በቃል፣ በስብሰባና በጽሑፍ በተደጋጋሚ ቢያቀርብም መፍትሄ ባለመሰጠቱ ችግሩ ተባብሶ በምርጫው ዕለት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደተገነዘበውና እንደተረዳው ድምጽ ለመስጠት የወጣው ሕዝብ በኢህአዴግ ካድሬዎች በደረሰበት ወከባና ጫና በነጻነት ድምፁን ለፈለገው ፓርቲ ሳይሰጥ ቀርቷል።

ለተቀመጠው ሕግ ባለን እምነትና በሕገ-መንግሥቱ ለተቋቋመው አካላት ባለን ከበሬታ ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት በማስረጃ አረጋግጠን ከምርጫው በፊትና በምርጫው ዕለት የተፈፀሙትን ግድፈቶች ገልፀን ለሁለተኛ ጊዜ ለኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ አቤቱታ ብናቀርብም እንደተለመደው ጉድለቱን በቦታው በመገኘት ሳያጣራ፣ በዝርዝር ሳይመረምር ማስረጃውን ሳይመዝን በደፈናው አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል።

የምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ከሚደነግገው ውጭ በቦርዱ ዋና ፀሐፊ በደብዳቤ የተሰጠንን መልስና ያሉንን ማስረጃዎች 232 ገጽ አያይዘን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበን በሁለተኛው ቀን አቤቱታ ካረቀብንበት መንፈስ ውጭ የምርጫ ቦርዱ በየደረጃው አቤቱታ አላቀረባችሁም ባላለበትና ጉዳዩን ተቀብሎ ያስተናገደን መሆኑ እየታወቀ በየደረጃው አላቀረባችሁም በማለት ከቀረበው ፍሬ ጉዳይ ውጭ አቤቱታችን ለክርክር ሳይቀርብ አያስቀርብም በማለት መልስ መስጠቱ ፍ/ቤቱ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ" ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

ምን ያህል ለጉዳዩ ትኩረት ያልሰጠው መሆኑን የሚያስረዳ ስለሆነ ወደ ቀጣዩ የሰበር ችሎት ጉዳዮን በመውሰድ አቤቱታ ለማቅረብ ተገደናል፡፡

መራጩ ሕዝብ በግልጽ እንደሚያውቀው ግንቦት 15/2002 ዓ.ም የተካሄደው ምርጫ ተቃዋሚዎች በተወዳደሩበት የምርጫ ክልሎች ሁሉ ምርጫው ፍትሐዊ፣ ነጻና ዲሞክራሲያዊ ሆኖ እንዳይጠናቀቅ እና ኢህአዴግ አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ በምርጫ አስፈጻሚዎች አጋዥነትና አይዞህ ባይነት በየደረጃው የሚገኙ ካድሬዎችና የአካባቢው ባለሥልጣናት ሳይታክቱ ከሕግ ውጭ ሰርተዋል፡፡ በመራጩም ሕዝብ ላይ ተጽእኖና ወከባ ፈጽመዋል፡፡

በገለልተኝነት ምርጫውን እንዲያስፈጽም የተቋቋመው የኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ በፍትሐዊነት፣ በእኩልነትና በሚዛናዊነት ሂደቱን ባለመከታተሉ በመጨረሻም በድምጽ አሰጣጡ ሂደት ላይ የደረሰውን ግድፈት ለመከላከል ባለመፈለጉ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲያዊ ትግል ላይ ከባድ ፈተና ደቅኖ አልፏል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት ለ19 ዓመታት በትክክል የሚያውቀው እውነት ባማረ ቃላት በማስጌጥና በምርጫ ስም የተደረገው ድራማ ፍትሐዊና ነጻ ምርጫ ተካሂዷል በማለት ምርጫ አስፈጻሚዎች በሕዝቡ የመምረጥ ዲሞክራሲያዊ መብት ላይ ተሳልቀዋል፡፡

በመላው አገሪቱ በተወዳደርንባቸው የምርጫ ክልሎች ከፍተኛ የምርጫ ግድፈት የተፈጠረ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም እነኚህን በሙሉ በዝርዝር በዚህ መግለጫ ማቅረብ አስቸጋሪ ስለሚሆን ከተፈፀሙት ግዙፍ ግድፈቶች ጥቂቶቹን ለግንዛቤ ያልህ ከዚህ በታች እንገልጻለን፡፡

## I. <u>አማራ ክልል</u>

1. ምንጃርና ሸንኮራ ምርጫ ክልል በህዝብ ታዛቢነት የተቀመጡት ግለሰብ የንብ ምልክት ያለበት ቲሸርት አድርገው ሂደቱን ይከታተሉ የነበረ ሲሆን ፖሊስ ደግሞ ክላሹን አንግቦ መራጩን ሕዝብ ንብ ላይ ምልክት እንዲያደርግ ሲያስፈራራው ይታያል፡፡ ይህንንም በወቅቱ ከተቀረፀው ምስል ማየት ትችላላችሁ፡፡

## II. <u>ደቡብ ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች</u>

1. ቦሎሳ ሶሬ ምርጫ ክልል 03 ምርጫ ጣቢያ ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት እንዳይታዘቡ በካድሬዎች ጫና ከመደረጉ በተጨማሪ ወጣቱን ወረፋ አለ በማለት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በቃላና ምርጫ ጣቢያ የተመዘገበው ህዝብ ብዛት 547 ሲሆን ኮሮጆው ሲከፈት የተገኘው የምርጫ ድምፅ መስጫ ወረቀት ግን 1152 ነው፡፡ በቦታው ለደረሰው ችግር ሁሉ ለምርጫ ኃላፊ ቢቀርብላቸውም ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡

2. በደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ምርጫ ክልል ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተካሄደው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትን ወክለው ለተወካዮች ም/ቤት የተወዳደሩት የምርጫው ሂደት ትክክል አይደለም በማለት ስለተናገሩ ማስፈራራት ደርሶባቸው ነበር፡፡ ወ/ሮ አማረች ገላኔ ግንቦት 21 ቀን 2002 ዓ.ም በአቶ በላቸው በየነ የፍርድ ቤት የጥበቃ ሠራተኛ በተተኮሰባቸው 23 ጥይት ተመትተው ሲገደሉ የ10 ዓመት ታዳጊ ህፃን ልጃቸው የሆነችው

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ"
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

ፀዳለች ገልገሎ በጀርባዋ ላይ በጥይት ተመትታ የቆሰለች ሲሆን ሌላው የ12 ዓመት ታዳጊ ህፃን ልጃቸው ፊይሣ ገልገሎ በሁለት ጥይት ጉልበቱ ላይ ተመትቶ ወላይታ ሶዶ ክርስቲን ሆስፒታል ተኝተው በመታከም ላይ ይገኛሉ። ሌሎች ሶስት ህፃናት በእናታቸው መሞትና በእህትና ወንድማቸው መቁሰል ምክንያት ተደናግጠው ከቤት እንደወጡ ተበታትነው ነው ያሉት።

III. **ኦሮሚያ ክልል**

1. **ዓለም ገና በሁለቱም የምርጫ ክልሎች**
   - ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በማስፈራራት፣ ድብደባ በመፈፀም፣ ከውድድር እንዲወጡ ከባድ ጫና ደርሶባቸዋል።
   - ለፓርቲያችን ታዛቢዎች መታወቂያ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሊሰጧቸው አልቻሉም።
   - ታዛቢዎቻችን መታወቂያ ከወሰዱም በኋላ ለስልጠና ትፈለጋላችሁ ብሎ የምርጫ አስፈጻሚው ካስጠራቸው በኋላ መታወቂያቸውን በመንጠቅና በመደብደብ እንዲባረሩ ተደርገዋል።
   - ተወዳዳሪዎችና ታዛቢዎቻችን በአካባቢው እንዳይገኙ ተደርገው ተወስደዋል።

ይህንን ሁሉ ተግባር የሚፈጽሙት የምርጫ ቦርድ አስፈጻሚዎችና የአካባቢው ባለሥልጣናት መሆናቸው በስምና በአካል የሚታወቁ ናቸው። ይህንኑ በአቤቱታችን ላይ ገልፀናል።

2. **በጉጂ ዞን /በለጋጉላ "ሀ" የምርጫ ጣቢያ**
   - ለመራጭነት የተመዘገበው ሕዝብ ብዛት 553 ሲሆን ለተወካዮች ም/ቤት የተሰጠው ድምጽ 5510 ሲሆን የሆነው ደግሞ 10 ነው። 4967 የምርጫ ወረቀት ተጭበርብሮ በኮሮጆ ውስጥ ተገኝቷል። ይህም የምርጫ ጣቢያው የድምጽ አሰጣጥ ሂደት እና የድምጽ ውጤት መግለጫ መተማመኛ ተረጋግጧል።

3. **በጉጂ ዞን በለጋሉላ "ለ" የምርጫ ጣቢያ**
   - ለመራጭነት የተመዘገበው የሕዝብ ብዛት 732 ለተወካዮች ም/ቤት ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተሰጠ ድምጽ 7940 ሲሆን ድምጽ አልባ 66 በትርፍነት የተገኘ ድምጽ 7274 ተጭበርብሮ በኮሮጆ ውስጥ ተገኝቷል። ይህም የምርጫ ጣቢያው የድምጽ አሰጣጥ ሂደት እና የድምጽ ቆጠራ ውጤት መግለጫ መተማመኛ ተረጋግጧል።

4. **በጉጂ ዞን ነገሌ የምርጫ ክልል/ቀበሌ 03 የምርጫ ጣቢያ**
   - ለመራጭነት የተመዘገበው ሕዝብ ብዛት 1098 ሲሆን ለተወካዮች ም/ቤት የተሰጠ ድምጽ 1035 ድምጽ አልባ 3 እና ድምጽ ያልሰጡ 144 መሆኑ ሲታወቅ በትርፍነት ተጭበርብሮ በኮሮጆ ውስጥ የተገኘ ድምጽ 84 ነው። ይህም የምርጫ ጣቢያ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት እና የድምጽ ቆጠራ ውጤት መግለጫ መተማመኛ ተረጋግጧል።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ"
ሥራ አመራር ጽ/ቤት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

## IV. በአዲስ አበባ ከተማ

- በሁሉም የምርጫ ጣቢያ በቡድን ሆነው በኔት ወርክ በሶስት የአደረጃጀት ዘዴ በቡድን ሆነው ከድምጽ መስጫ ጣቢያ በር ጀምሮ ሕዝቡ ወደ ምርጫ የሚመጣባቸውን ቁልፍ ቦታዎች ላይ በመሆን ኢህአዴግን ምረጡ በማለት ማስገደድ ፈቃደኛ ያልሆነው የማስፈራራት ተግባር ሲፈጽሙ ውለዋል፡፡
- በወረዳ 12/13 የምርጫ ክልል በቀበሌ 06/07/19 ለ የምርጫ ጣቢያ ለምርጫ የተመዘገበ ሕዝብ ብዛት 789 ሲሆን የመረጠው 889 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በልዩነት 74 ድምጽ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡
- በወረዳ 6 የምርጫ ክልል በምርጫ ጣቢያ 51 ለምርጫ የተመዘገበው ሕዝብ ብዛት 423 ሲሆን የመረጠው ብዛት 523 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በልዩነት 100 ድምጽ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

**አንዲት ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!**

**የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ"**




ሰኔ 15/2002 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>